# የሠለሐዲን መስጂድ

## የሦስት የተሻለ ዕድሎች ባለቤት የሆነ መስጂድ

<u>የተመሰረተበት ዘመን:-</u> በ1938

<u>የሚገኝበት አካባቢ:-</u> ኳስ ሜዳ፣ ከዋናው የአስፋልት መንገድ አጠገብ

<u>የሥሙ ሥያሜና ትርጉም:-</u> መስጂዱ ለረዥም ዓመታት ሐጂ ዩኑስ መስጂድ ሲባል ነበር:: ኋላ ግን ሰዎች በመናብ አየን ያሉትን ለሐጂ ዩኑስ ይነግሯቸዋል:: ይህም አንድ የታወቁ ሸኽ ሰለሃዲን የተባሉና በሀረር የሚገኙ ዓሊም መቃብራቸው መንገድ ዳር የሆነ «ሰዎች ሽንት እየሸኑ አስቸገሩኝ:: ከዚህ በኋላ ሐጂ ዩኑስ መስጂድ ገብቻለሁ» ብለው ማሳወቃቸውን ነገሯቸው:: ከዚህ በኋላም የመጀመሪያ ማህተም ተቀይሮ አዲስ ማህተም በማስቀረጽ ሰለሃዲን መስጂድ መባሉ የመረጃ ምንጮቻችን ያስረዳሉ::

<u>መግቢያ:-</u> ስለ ሰለሃዲን መስጂድ ታሪክ ለመፃፍ ስዘጋጅ ከዚህ ቀደም በአካባቢው ለተወሰነ ጊዜ ስኖር የተመለከትኩትን የረመዳን ወር ትዝታ መጣብኝ:: የኳስ ሜዳና የሰለሃዲን መስጂድ በረመዳን ወር የ24 ሰዓት አገልግሎትና እንቅስቃሴ አላቸው ቢባል የተጋነነ አይደለም:: ከ1984-1987 አካባቢ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ በኳስ ሜዳ አካባቢ ቤት ተከራይቼ ስኖር እንደማስታውሰው «ረመዳን ወር በኳስ ሜዳ» ራሱን የቻለ አንድ መጽሐፍ ሊያጽፍ የሚችል ነው:: ረመዳን ሲገባ በአካባቢው ሣር ቅጠሉም «ረመዳን-ረመዳን» የሚል ከመሆኑም በላይ እንቅስቃሴው ያለ ማቋ ረጥ 24 ሰዓት የመቀጠሉ ጉዳይ ደግሞ ያስገርማል:: ለምሣሌም በሱሁር ሰዓት ዳቦ ገዝቼ ልግባ ቢሉ ያገኛሉ:: እንደኔ አይነቱ ወንደላጤ ደግሞ ለሱሁሩ ያዘጋጀው ባይኖር ወጣ ብሎ በመስጂዱ አቅራቢያ በነበሩ ሻይ ቤቶች ቀማምሶ ወደ ቤቱ ሊመለስ ይችላል:: ሌላው ቢቀር እርጎና ዳቦ የማያጡ እነዚሁ ሻይ ቤቶች ገበያቸው ከተራዊህ በኋላ ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ለሊቱ 11 ሰዓት ነበር ማለት ይቻላል::

ኳስ ሜዳ አካባቢ ሌላው ትዝታው ሶስት መስጂዶች በቅርብ ርቀት የሚገኙበት መሆኑ ነው:: ሰለሃዲን መስጂድ በመሀል ይሆንና በስተሰሜን በኩል አቡበክር

ሲዲቅ (ሐጂ ዘይኑ) መስጂድ ሲገኝ፣ በስተምስራቅ አቅጣጫ ደግሞ የሀሺም መስጂድ ይገኛል:: እዛ አካባቢ ካሉ የሶስቱም መስጂዶች አዛን ይሰማሉ:: በተለያዩ መስጂዶች መስገድ አጅር አለውና ዙሁርን፣ አስርን፣ መግሪብንና ኢሻን አፈራርቄ ልስገድባቸው ቢሉ ያመችዎታል:: የኳስ ሜዳ አካባቢ ረመዳን ወርን የሚያሞቀው አንዱ ምናልባትም ዋንኛው የነዚህ መስጂዶች ቅርብ ለቅርብ በመኖራቸው ሳይሆን አይቀርም::

አንዲት ትዝታዬን ጨምሬ መግቢያዬን ልቋጭ:: መቼም ከ1984-1987 በኳስ ሜዳ በኖርኩበት ዓመታት አንድ ሚስኪን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበርኩና «ውለታዋ» እስካሁን የማልረሳው በሰለሃዲን መስጂድ አጠገብ አንዲት ሥጋ ቤት ነበረች:: ምን የመሰለ ቀይ ወጥ በሁለት ብር ትሸጥ ነበር:: መቼም እኔና አህመድ ጀማል የተባለ ጓደኛዬ ዋና ደንበኛዋ ነበርን:: ቆይታ ግን 0.50 ሣ.ም በመጨመር 2 ብር ከ 50 ሣ.ም ሆነች:: በዚህም ምክንያት በዛብንና ደንበኝነታችንን መቀነሳችን ትዝ ይለኛል:: ሰሞኑ እዚህ ታሪክ ዳሰሳ አጋጣሚ ጎራ ልል ስፈልጋት ሱቅ ሆና አገኘኋት::

<u>አመሰራረት:-</u> የዚህ መስጂድ የአመሰራረት ታሪክ በቀጥታ ሐጂ ዩኑስ አህመድ ከተባሉ ሰው ጋር የተያያዘ ነው:: ሐጂ ዩኑስ የሀረሪ ተወላጅ የነበሩ ሲሆን ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በፒያሣ፣ አወሊያ ት/ቤት ፊት ለፊት በሚገኘው የድሮ ማስታወቂያ ሚኒስቴር አጠገብ ታዋቂ የልብስ ስፌት ድርጅት ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን ያቋቁማሉ:: በዚህም ድርጅታቸው የመንግስት ዩኒፎርሞችን በተለይም የፖሊስ፣ የጦር ሠራዊት፣ የክብር ዘበኞች...ዩኒፎርሞችን በጨረታ በመውሰድና በመስራት የታወቁና ቁጥር አንድ ሆነው የሚገለፁ ይሆናሉ:: እኚህ ሰው በመጀመሪያ በጣሊያን ሠፈር ይኖሩ የነበረ ሲሆን በኋላም አሁን መስጂዱ ያለበት አካባቢን ገዝተው ቤት መስርተው ይገባሉ:: ቤታቸው አሁንም ከመስጂዱ በር ፊት ለፊት የሚገኝ ሲሆን ልጆቻቸው ይኖሩበታል::

ሐጂ ዩኑስ ወደዚህ አካባቢ መጥተው መኖር ከጀመሩ በኋላ የጀመአና የጁመአ ነገር ያሳስባቸዋል:: በጊዜው ደግሞ በአካባቢው ብዙም ሰው ያልነበረ፣ እልም ያለ ጫካና ጥሻ የበዛበት ነበር:: በመሆኑም ወዳጆችን ለመሳብ፣ ጀመአንና ጁመአን ለማቋቋም ሲሉ መስጂድ መመስረት እንዳለባቸው ይረዳሉ:: ወዲያውኑም ከቤታቸው ፊት ለፊት ያለውንና አሁን መስጂዱ ያለበትን ቦታ





በ500 ብር ገዝተው ለመስጂድ ይወቅፉታል:: የዛን ጊዜ 500 ብር የዛሬ ስንት ሺህ ብር እንደሚሆን እናንተው አስሉት::

<u>ታሪካዊነት:-</u> ሰለሃዲን መስጂድ በ1938 የተቋቋመ በመሆኑ ከአዲስ አበባ መስጂዶች ታሪክ አንፃር ከቀደምቶች አንዱ ያደርገዋል:: ይህ ከሆነ ሰለሃዲን መስጂድ ከታሪካዊ ቅርስነት አንፃርም ሊጠቀስና ሊገለጽ ይችላል ማለት ነው:: በመሆኑም አንድ የቅርስ ክፍል ሊኖረውና ያሉትን ቅርሳ ቅርሶች ተጠብቀው ለትውልድ የሚተላለፉበት መንገድ መቀየስ ተገቢ ነው:: ለምሣሌም በ1946 የተሰጠ ካርታ ለመመልከት ችያለሁ:: ይህም ምናልባት በአዲስ አበባ መስጆደች ታሪክ የመጀመሪያው ካርታ ሣይሆን ይቀራል? አለን ሊሉ የሚችሉት ወሌ መሐመድ፣ ኑርና አንዋር ናቸው:: ካለ ተሰባስቦ መቀመጥ አለበት:: ይህ ብቻ ሳይሆን መስጂዱ 64 ዓመቱ የሆነው በመሆኑ የ65 ዓመት <u>እዮቤልዩ</u> በዓሉን በሚቀጥለው ዓመት ቢያከብር ብዙ ልማታዊና ታሪካዊ ሥራዎች ሊሰራበት ይችላል:: በዚህ ጉዳይ ኮሚቴዎች እንዲያስቡበት እናስታውሳለን:: አስፈላጊ ከሆነም እኛም ልናግዛቸው እንችላለን::

<u>የአመሰራረት ውጣ ውረድ:-</u> እንኳን በዛ ዘመን በአዔው ግፍ የበዛበትና እኩልነት ባልነበረበት ጊዜ ቀርቶ በአሁኑ ጊዜ እንኳ ቢሆን መስጂድ ለመመስረት የሚያስከፍለው መስዋዕትነት እጅግ የበዛ ሆኖ ይገኛል:: የሰለሃዲን መስጂድ በ1938 በሐጂ ዩኑስ አህመድ ከላይ በምስረታው ላይ እንደተገለፀው ሲቋቋም ቀላል የማይባል ውጣ ውረድና ችግሮች ገጥመውት ነበር:: ዋናውና ትልቁ ውጣ ውረድ ከባለስልጣናት በኩል የነበረው ጫና ነበር:: ሐጂ ዩኑስ መስጂዳቸው ህጋዊ እንዲሆን ከምስረታው ጀምረው ይለፉ ነበርና የመንግስት አካላት ሕጋዊነቱን ለመቀበል በጣም ተቸግረው ነበር:: ሐጂ ዩኑስ ለከፍተኛ የመንግስት ተቋማት ዩኒፎርም ሰፊ ድርጅት የነበራቸው . ታዋቂ ሰው በመሆናቸውና በብዙ የብር ኃይል ተቋቋሙት እንጂ «በመብትነት» የሚገኝ ስለመሆኑ የሚታሰብ አልነበረም:: በጊዜው ለመስጂድ ሕጋዊ ፈቃድ መስጠት በመንግስት እንደ ኃጢያትና ወንጀል የሚቆጠር እንደነበር የታሪክ ምንጮቻችን ያስረዳሉ:: በዚህ የተነሣ መስጂዱን ለማቋቋም ከተከፈለው ብዙ የሚበልጥ ገንዘብ ለባለስልጣናትና ለሹማምንት እንደጠፋ ይገልፃሉ::

ሌላኛው በምስረታ ወቅት የነበረው እንቅፋት በመስጂዱ አጠገብ አንድ ጠንቋይ እንደነበር የሚያስታውሰው ታሪክ ነው:: ጠንቋዩ የመስጂዱ መቋቋም ሲያውቅ

ችግር መፍጠር ጀመረ::: በተለይ የሚያውቀውን ሁሉ በማድረግ ጂንና ሸይጧን በመጥራት ቀውስና ውዥንብር ለመፍጠር ሞከረ:: ሐጂ ዩኑስ ለጂን መከላከያ የሚባሉትን የቁርአን አንቀጾችን በመቅራት ለመቋቋም ሲሞክሩ ከቆዩ በኋላ በመስጂዱ አዛን ሲጀመር ጠንቋዩ አካባቢውን ለቆ ለመሄድ መገደዱ ይነገራል::

<u>የመስጂዱ የዕድገት ደረጃዎች:-</u> በ1938 ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው መስጂድ ግርግዳው በእንጨትና በጭቃ፣ ጣራው ቆርቆሮ የነበረ ነበር:: ስፋቱም በግምት ከ70-80 ሰዎችን ሊይዝ የሚችል እንደነበር ይነገራል:: በ1950 ዎቹ ላይ ደግሞ በአጠገቡ የነበረ ቦታ በድጋሜ ተገዝቶ በመጨመር መስጂዱም ፈርሶ ሰፍቶ ተገነባ:: ለሁለተኛ ጊዜ የተሰራው መስጂድ ስፋቱ በግምት 6 X በ12 ሜትር አካባቢ የሆነ ነበር:: አሰራሩም በጊዜው በጣም ጠንካራና ውብ በነበረው በአሸዋ ግርፍ የተሰራ ነበር:: መስጂዱ ለሶስተኛ ጊዜ የለውጥና የዕድገት ዕድለኛ ሆኖ በ1970ዎቹ ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ተሻሽሎ በአዲስ መልክ ለመገንባት ችሏል:: ይህንን ግንባታ ያካሄዱት ታዋቂው አህለል ኸይር ሐጂ ቱሬ ናቸው:: አላህ ለጀነት ያርጋቸው:: ይዞታውንም በግገር በማስፋትና አሁን የሚታየውን መስጂድ በማስገንባት ላቅ ያለ አስተዋጽኦ አድርገውለታል::

<u>መስጂዱ አሁን ያለበት ደረጃ:-</u> በአሁኑ ጊዜ መስጂዱ በድንጋይና በብሎኬት የተገነባና ውስጡም ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ የተነጠፈ ነው:: መስጂዱ ያረፈበት ስፋት 413 ካ.ሜ ላይ ነው:: የሴቶች መስገጃም አለው:: የአንድ ረኸዐም ሚናራ ባለቤትም ነው:: የሚናራው ቁመት ግምቱ ባይገኝም መለሎ ሆኖ ይታያል::

<u>የሰጋጁ ብዛት:-</u> የወንድና የሴት መስገጃው ተጨምሮ በአንድ ጊዜ ወደ 1000 ሰዎችን ሊያስተናግድ ይችላል::

<u>የመስጂዱ የይዞታ ስፋት:-</u> በአሁኑ ጊዜ ያለው የይዞታ ስፋት 629 ካ.ሜ ቦታ ነው:: ይህም በሶስት ጊዜ ግገር የሰፋ ነው:: የመጀመሪያው 343 ካ.ሜ ስፋት ነበረው:: በ1950ዎቹ ትንሽ ተጨምሮበት ሰፍቷል:: እንደገናም በ1970 ዎቹ ሐጂ ቱሬ አሁን የሚታየውን መስጂድ ሲገነቡ የተወሰነ ስፋት ገዝተው ጨምረውበታል:: አሁን ለአራተኛ ጊዜ መስፋት ይፈልጋል:: ከ1973 ጀምሮ ለመንግስት ያቀረበው ጥያቄ አለ::

<u>አጥር:-</u> የመስጂዱ ይዞታ በግንብ የታጠረ ነው::





<u>ካርታ:-</u> ሰለሃዲን መስጂድ በሚያዝያ 16 ቀን 1946 ላይ የተሰጠ ካርታ አለው:: በዛን ጊዜ የነበረው የቦታ ስፋትም 343 ካ.ሜ ሆኖ ይገኛል:: በዛን ጊዜ እንዴት ካርታ ሊያገኝ ቻለ? ከሱ በፊትስ ካርታ ያገኙ መስጂዶች ይኖሩ ይሆን? ብዙ የሚያመራምር ነው:: በጊዜው ካርታ የማግኘቱ ጉዳይ ያለ ምንም ጥርጥር የመስራቹ የሐጂ ዩኑስ አህመድ ችሎታ፣ ጥረትና ትግል ነው:: እኚህ ሰው አስተዋይ ሰው ስለነበሩ በጊዜው የነበረውን ከፍተኛ ፈተና እንደምንም ብለው በማለፍ መስጂዱ ካርታ እንዲኖረው አድርገውታል:: በአሁኑ ጊዜም በ10/9/1998 የተሰጠው ካርታ ይዟል:: በዚህም ካርታ የቦታው ስፋት 629 ካ.ሜ ሆኖ ተጽፏል::

<u>መድረሣ:-</u> ከመስጂዱ እድሜ እኩል ታሪክ ያለው መድረሣ አለው:: አሁን ያለበት ደረጃም ከመስጂዱ ጋር በግንብ የተገነባ ሆኖ ሁለት ክፍሎች አሉት:: ወንበርና ጠረጴዛዎች አሉት:: ወደ 150 ደረሶች ይማሩበታል:: በዋነኝነት የቁርአን ትምህርት ይሰጥበታል:: ከምስረታው እስካሁን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ደረሶች የተመረቁ ቢሆንም መረጃው ስላልተያዘ ለማወቅ አልተቻለም:: ለወደፊቱ ግን በየመድረሣዎቻችን የሚመረቁ ደረሶች ሥምና ቁጥር መዝግቦ መያዝ ከመድረሣዎቻችን ሁሉ የሚጠበቅ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንወዳለን::

በሰለሃዲን መስጂድ መድረሣ ከወጡ ታላላቅ ሰዎች ውስጥ አምባሳደር ተውፊቅ ሸኖ ይጠቀሳሉ:: አምባሳደር ተውፊቅ በአሁኑ ጊዜ በየመን የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን በማገልገል ላይ ናቸው::

<u>የኢልም ፕሮግራሞች:-</u> ከመግሪብ እስከ ኢሻ ቁርአን፣ ተፍሲርና ተጅዊድ ይሰጣል:: ጠዋት ከሱብሂ በኋላ ደግሞ ተውሂድ፣ ፊቂህና ሀዲስ ይሰጣል::

<u>የገቢ ምንጮች:-</u> ምንም የለውም:: ለወደፊቱ የታቀደው የቦታ ማስፋት እቅድ ከተሣካ አያሌ የገቢ ምንጭ የሚሆኑ እድሎች ስላሉት እቅዱን ማስፈፀም የአላህ በመቀጠል የሠጋጁና የኮሚቴዎች ሁሉ ተሳትፎን ይጠይቃል::

<u>ኢማሞች:-</u> ሰለሃዲን መስጂድ አያሌ ድንቃ ድንቅ ታሪኮች አሉት:: እስካሁን ሁለት ድንቅ ታሪኮቹን ተመልክተናል:: አንደኛው በ1938 የተመሰረተ በመሆኑ ከምስረታ አኳያ ቀደምትነት ካላቸው የአዲስ አበባ መስጂዶች አንዱ መሆኑ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ምናልባትም ከአዲስ አበባ መስጂዶች የመጀመሪያው

ካርታ ያገኘ ሊያሰኘው የሚችል በ1946 የተሰጠው ካርታ መያዙ ነው፡፡ አሁን ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ ከአዲስ አበባ መስጂዶች ሁሉ ልዩ ክስተት የሆነ ነገር ልናወሳ ነው፡፡ ይህም የኢማሙ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ነው ክርእሳችን በታች መስጂዱ የሶስት ልዩ አትኩሮትና አክብሮት የሚሰጣቸው ዕድሎች ባለቤት ያልነው፡፡ መስጂዱ በ1938 ሲመሰረት የነበሩት ኢማም እስካሁን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ሥማቸው ሐጂ አብዱልጀሊል ሙሐመድ ይባላል፡፡ ላለፉት 64 ዓመታት መስጂዱን በኢማምነት መርተዋል፡፡ አሁንም በመምራት ላይ ይገኛሉ፡፡ መስጂዱ በሚቀጥለው ዓመት (በ2003) የ65 ዓመት እዮቤልዩን ካከበረ የርሳቸውም የ65 ዓመታት የኢማምነት አገልግሎት እዮቤልዩአቸውን ተያይዞ ሊያከብሩና ሊከበር ይችላል፡፡

መቼም እንዲህ አይነት የጊዜ ክስተቶች በአግባቡ ለሚጠቀምባቸው ሰው ራሳቸውን የቻሉ ኃብትና ንብረት ናቸው፡፡ የሰለሃዲን መስጂድም ይህንን ዕድሉን በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡ አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ እኛም ለመስጠት ዝግጁ ነን፡፡ ሌሎችም መስጂዶች የ50 ዓመት፣ የ75 ዓመት፣ የ100 ዓመታት እዮብልዩዋቸውን ለማክበርና በዓሉንም ለልማታቸውና ለዕድገታቸው ለመጠቀም ሲፈልጉ ከጎናቸው ሆነን የምንሰራ መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ እናስታውቃለን፡፡

**ሙአዚኖች (የሰላት ጥሪ አድራጊዎች) ፡-**

1. ሸኽ አው ያህያ
2. ሐጂ አወል ሙሐመድ
3. ሙአዚን ኑሬ
4. ሌሎች
5. ሐጂ ሀሩን ዩኑስ
6. ኡስታዝ ጀማል ሙሃጅር

**ተወዳጅነትና ተሰሚነት፡-** ኢማሙ ሐጂ አብዱልጀሊል መሐመድ ለ64 ዓመታት በኢማምነት፣ ልጆችን ቁርአን በማስተማርና በምክር ስላገለገሉ ለዚህ ደረጃና ክብር በቅተዋል፡፡

**ኮሚቴዎች፡-**

1. ሐጂ ሀሩን ዩኑስ. . . . . . . . . . . . . . . . .ሰብሳቢ
2. ሐጂ ዩሱፍ ኢብራሂም. . . . . . . . . . . . . . .ገ/ያዥ
3. አቶ መካሪም ያሲን . . . . . . . . . . . . . . . . ፀሃፊ
4. አቶ ኢሣ አህመድ. . . . . . . . . . . . . . . . . .ሂ/ሹም





5. አቶ ኑረዲን ቢላል . . . . . . . . . . . . . . . . ን/ክፍል

**የመስጂዱ የወደፊት ራዕይ፡-** መስጂዱ በአንድ ወሳኝ በሆነ የዕድገት ራዕይ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም በ1973 የተጀመረ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች የተጓተተና ተግባራዊ ያልሆነ ነው፡፡ በ1973 የእስልምና ጉዳዮች ም/ቤትና የመስጂዱ ኮሚቴዎች ባደረጉት ጥረት በመስጂዱ ዙሪያ የሚገኙትን ቦታዎች በመጠቀም ለማስፋፋትና ልማቱን ለማጠናከር ለመንግስት ቀርቦ በቅድመ ሁኔታ ደረጃ ተፈቅዶ ነበር፡፡ ቅድመ ሁኔታውም «ለሚነሱት ሰዎች ግምት ወጪ ለመሸፈን መስጂዱ ከቻለ» የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን በተለያዩ የውስጥ ድክመቶች እስካሁን (ይህ እድል) ተግባራዊ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ አሁን ያሉት ኮሚቴዎች ግን ይህን እድል ለመጠቀም ቆርጠው ተነስተዋል፡፡

በመስጂዱ ዙሪያ ከዋና የአስፋልት መንገድ ጋር በተያያዘ አያሌ ቤቶችና ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ይህም የተቻለውን ሁሉ መስዋዕትነት ተከፍሎበት ለመስጂዱ የወደፊት ዕድገት ልማት ቢውል ከፍ ያለ ሀገራዊ፣ ዲናዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በጣም ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡፡ የመስጂዱ ኮሚቴዎች፣ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤትና ሌሎችም ድጋፍ ለማድረግ ዕድሉ ያላቸው ሲጋጆች ሁሉ ብርቱ ተሳትፎአቸው ይጠበቃል፡፡ ለዚህና ለሌሎችም የወደፊት ዕድሎችና ድሎች መስጂዱ በ2003 የ65 ዓመት እዮቤልዩን በማክበር ድጋፍ ማሰባሰብና ማጠናከር እንደሚኖርበት እናምናለን፡፡

**የመረጃ ምንጭ፡-**

1. የመስጂዱ ኮሚቴዎች
2. ሐጂ አብዱልጀሊል መሐመድ

**የስልክ አድራሻ፡-**

**011-2-13 68 51**